# ዜና መድን
# (Zena medin)

# ድርጅታችን ዓለም ዓቀፍ የሒሳብ ሪፖርት ደረጃዎችን (International Financial Reporting Standards) በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡

የተለያዩ ሀገራት እንደየሀገራቸው ሕግ እና ስርዓት የተለያዩ የሒሳብ አመዘጋገብ እና ሪፖርት አቀራረብ ስርዓት (Local GAAP) ተግባራዊ ሲያደርጉ መቆየታቸው ይታወቃል፡፡ ይሁንና ይህ አሠራር የተለያዩ ተቋማትን የፋይናንስ ሪፖርት ለማወዳደር ወይም ለማነጻጸር አስቸጋሪ በመሆኑ ለንደን የሚገኘው የ ዓለም አቀፍ የሒሳብ አያያዝ ደረጃዎች ቦርድ (International Accounting standards Board) ዓለም አቀፍ የሒሳብ ሪፖርት ደረጃዎችን (International Financial Reporting Standards) እያወጣ ይገኛል፡፡

በአገራችን ኢትዮጵያም ወጥ የሆነ የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት እና አቀራረብ ሕግ መኖሩ ያልተማከለ የነበረውን የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት እና አቀራረብ ማማከል ግልጽነት እና ተጠያቂነት የሚያጎለብት መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት እና አቀራረብን በኃላፊነት ለመምራት እና ለመቆጣጠር ስልጣን የተሠጠው የኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ (Accounting and Auditing Board of Ethiopia) በአዋጅ ቁጥር 847/20006 እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡ በአዋጁም መሠረት የህዝብ ጥቅም ያለበት አካል፤ ኢንሹራንስ ድርጅቶችን ጨምሮ፤ ዓመታዊ

የሒሳብ መግለጫ ወይም ሌላ የሒሳብ ሪፖርት ሲያዘጋጁ ዓለም አቀፍ የሒሳብ ሪፖርት ደረጃዎችን መከተል እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡

የኢትዮጵያ መድን ድርጅትም የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ ባስቀመጠው አቅጣጫ መሠረት የፋይናንስ ሪፖርቱን በዓለም አቀፍ የሒሳብ ሪፖርት ደረጃዎች መሠረት አማካሪ ድርጅት ቀጥሮ እንዲሁም በውስጥ የፕሮጀክት ቡድን አቋቁሞ በመስራት ላይ ይገኛል፡፡ በዚህም መሠረት ድርጅታችን የሁለት ዓመታት የሒሳብ መግለጫ በዓለም አቀፍ የሒሳብ ሪፖርት ደረጃዎች መሠረት ተዘጋጅተው ኦዲት ለማስደረግ የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ መገኘቱን ከፕሮጀክት ቡድኑ ያገኘነው መረጃ ያመለክታል፡፡

በቀጣይም ድርጅታችን የፋይናንስ ሪፖርት በዚሁ የዓለም አቀፍ የሒሳብ ሪፖርት ደረጃዎች መሠረት የሚያዘጋጅ በመሆኑና ስራውም የሁሉንም ክፍሎች ትብብር የሚጠይቅ በመሆኑ የስራውን ውጤታማነት ለማረጋገጥ ይረዳ ዘንድ ለሁለት ቀናት ማለትም እ.ኤ.አ ከሚያዚያ 8 እስከ 9 2019 ዓ.ም በኢንተር ኮንቲነንታል ሆቴል ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የድርጅቱ የስራ ዓመራር ዓባላት በአማካሪው ቡድን በኩል የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና  የተሠጠ ሲሆን፤ የሪፖርት አዘገጃጀት ስርዓቱ በድርጅቱ ላይ የሚያመጣውን ለውጥ እንዲሁም ለሪፖርት አዘገጃጀቱ ውጤታማነት ከተለያዩ የስራ ክፍሎች የሚጠበቀው ኃላፊነት ምን እንደሚመስልም ውይይት ተደርጓል፡፡

# ለድርጅቱ ሠራተኞች ስልጠና ተሰጠ

## የተለያዩ አጫጭር ሥልጠናዎች ተሰጡ

**በኢትዮጵያ መድን ድርጅት ለተለያዩ የድርጅቱ ሠራተኞች እ.ኤ.አ. ከጥር 1 እስከ መጋቢት 30 ቀን 2019 ድረስ በድርጅቱ የስብሰባ አዳራሽ፣ በፋይናንስና ጥናት አካዳሚ እና በሌሎች ድርጅቶች አማካኝነት** በአጠቃላይ ለ168 ሠራተኞች **የተለያዩ ሥልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡ በዚህም መሠረት፡-**

- **ውስጥ ለውስጥ የተሰጡት ሥልጠናዎች፡-**

- እ.ኤ.አ. ከጥር 21 – 28, 2019 **ለ5 ሠራተኞች በ**" Crain Operators" ላይ፣
- እ.ኤ.አ. ከየካቲት 25-መጋቢት 15 2019 ለዘጠኝ ሠራተኞች በ" Record Management" ላይ፣
- እ.ኤ.አ. ከመጋቢት 11-15 2019 ለ17 ሠራተኞች በ" Cashiers training" ላይ በአጠቃላይ ለ30 ሠራተኞች ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡

**በፋይናንስ ጥናት አካዳሚ የተሰጡት ስልጠናዎች፡-**

- እ.ኤ.አ. ከጥር 21- 25, 2019. ለ9 ሠራተኞች በ" Marine Insurance " ላይ፣
- እ.ኤ.አ. ከጥር 28 – 31, 2019 ለ14 ሠራተኞች በ" Insurance Accounting " ላይ፣
- እ.ኤ.አ. ከየካቲት 18 – 22, 2019. ለ9 ሠራተኞች በ" Property & Pecuniary Insurance " ላይ፣
- እ.ኤ.አ. ከመጋቢት 18 - 22 2019. ለ7 ሠራተኞች በ" Motor Insurance" ላይ፣
- እ.ኤ.አ.ከመጋቢት 25 – 29, 2019 ለ10 .ሠራተኞች በ" Contractor & Engineering Insurance " ላይ በአጠቃላይ ለ49 ሠራተኞች ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡

### በሌሎች ድርጅቶች የተሰጡ ስልጠናዎች

* እ.ኤ.አ. ከጥር 28-የካቲት 1/2019 ለ 3 ሠራተኞች በ" 3rd round Industry training" ላይ በ **Association of Ethiopian Insurers** አማካይነት ፣
* እ.ኤ.አ. መጋቢት 13/2019 ለ2 ሠራተኞች በ" Political Violence Insurance Underwriting & Claims Handling " ላይ በ **Ethiopian Reinsurance S.C.** አማካይነት ፣
* እ.ኤ.አ. ከሚያዚያ 4-5 /2019 ለ4 ሠራተኞች በ" Underwriting Political Violence & Terrorism Risk" ላይ በ **Society of Insurance Professionals** አማካይነት ፣

* እ.ኤ.አ. ከመጋቢት9-11/2019 ለ1 ሠራተኞች በ" Women's, Youth & Children Issue Forum " ላይ በ FDRE Public enterprise Holding & Administration Agency አማካይነት በአጠቃላይ ለ10 ሠራተኞች ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡

በአጠቃላይ በ3ኛው ሩብ ዓመት ውስጥ 89 ሠራተኞች ስልጠና የተሰጠ መሆኑን ከሀብት አስተዳደር ስልጠና ማዕከል ያገኘነው መረጃ የመለከታል፡፡



ሔለን አበራ
ዋናው/መ/ቤት
ተላላኪ
እ.ኤ.አ ከመጋቢት 25 ቀን 2019



ሰሚራ ኑሬ
ህይወት አዲስ ዲስትሪክት
ተላላኪ
እ.ኤ.አ ከመጋቢት 25 ቀን 2019



እየሩሳሌም መኮንን
ቃሊቲ ቅርንጫፍ
ተላላኪ
እ.ኤ.አ ከመጋቢት 25 ቀን 2019

# በጡረታ የተሰናበቱ

**እ.ኤ.አ ከጥር 1 ቀን 2019 እስከ መጋቢት 31 ቀን 2019**

## ከድርጅቱ በጡረታ የተሰናበቱ ሰራተኞች

ገነት ቦጋለ
ጽዳት እ.ኤ.አ ጥር 9 ቀን 2019

ድሬዳዋ ዲስትሪክትዋ/መ/ቤት
ኮሌክተርእ.ኤ.አ ጥር 9 ቀን 2019

የኢንተግሬትድ ኮሚዩኒኬሽን ቡድን አባላት ወደ ድርጅታችን ለተቀላቀሉት ሠራተኞች መልካም የስራ ዘመን እንዲሆንላችሁ እየተመኛ! በጡረታ ለተሰናበቱት ሠራተኞችም መልካም የእረፍት ጊዜ እንዲሆንላችሁ ልባዊ ምኞቱን ይገልፃል!!!

የኢትዮጵያ መድን ድርጅት የውስጥ መጽሔት የሆነችውን የዜና መድን መጽሔት ስላነበባችሁ ከልብ እያመሰገን ስለ መጽሔቷም ሆነ በአጠቃላይ ስለ ድርጅቱ ያላችሁን አስተያየት በድርጅቱ የኢ.ሜይል አድራሻ bdrm@eic-et.com አዲስ በተዘረጋው የኔትወርክ አገልግሎት እንዲሁም በፖስታ ሣ.ቁ. 2545 ለኢንተግሬትድ ኮሚዩኒኬሽን ቡድን በሚል እንድትልኩልን በአክብሮት እንጠይቃለን፡፡

እናመሰግናለን!!

ኢንተግሬትድ ኮሚዩኒኬሽን ቡድን